# በክርስቶስ ያገኘነው ማንነት

## ማንነትን ማወቅ ይጠቅማልን?

``ስለ ነገሮች የምናውቀው እውቀት እጅግ በጣም አስፈላጊ ቢሆንም ማን መሆናችንን ማወቅ ባጣም የላቀ እውቀት ነው፤ ምክንያቱም ማንነትን ማወቅ ራስን ማወቅ ነው፤ ራስን ማወቅ የተፈጠርንለትን አላማ ማወቅ ነው፤ የተፈጠርንለትን አላማ ማወቅ አካሂያዳችንን ማሳመር ነው`` [1]ብሬኒ ብራውን

## የተለመዱ መጠይቆች[2]፡-

- እኔ ማን ነኝ? (ማንነት)
- ከየት መጣሁ? (ምንጭ)
- እዚህ (በምድር) ያለሁት ለምንድን ነው? (አላማ)
- ምን ማድረግ እችላለሁ? (አቅም፤ ክህሎት)
- ሕይወቴ ወዴት እየሄደ ነው? (ፍጻሜ)

ከላይ የተነሱትን ጣያቄዎች መመለስ ተገቢ ቢሆንም የጽሑፌ ትኩረት ግን አይደለም፡፡ ስለዚህ ለአንባቢው ተትተዋል፡፡

---

[1] ዮዲት ታሪኩ፤ ማንነት በመጽሐፍ ቅዱስ አውድ፡ በክርስቶስ ያለን ማንነት፤ የፕሮግራም ንግግር፤ Selah Ethiopia: YouTube Channel.

[2] Myles Munroe, Dr . 5 Questions every Human being must answer. Wordpress.com

ሳይንስ ስለ ሰዎች ማንነት ብዙ ጥናት አቅርቦአል፤ ግን በቂ አይደለም። የሰውን ማንነት የማስተማር ሙሉ አቅም ያለው የእግዚአብሔር ቃል ነው። ለምን? ስሪታችን በትክክል የተጻፈው በቃሉ ስለሆነ።

**ቃሉ ማንነታችንን እንድናውቅ ያበረታታል?** አዎ።

``ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን?`` 1ኛ ቆሮንቶስ 6፡19

በዚህ ክፍል ``አታውቁምን?`` የሚለው አገላለጽ ማወቅ እንደነበረባቸው የሚገልጽ ነው። አማኞቹ ማንነታቸውን አውቀው፣ ለማንነታቸው የሚመጥን ኑሮ መኖር ይጠበቅባቸዋልና። ንጹህ ኑሮ የሚቀዳው ማንነትን ማለትም በክርስቶስ የተደረግነውን ወይም የሆንነውን ከማወቅ ነው።

## በክርስቶስ ያለንን ማንነት የማወቅ ፋይዳ

``እኛ በክርስቶስ ኢየሱስ ማን ነን? እግዚአብሔር ያዳናቸው አማኞች ማንነታቸው ምንድን ነው? ትልቅ ወሳኝ ጥያቄ ነው፤ `እኔ ማን ነኝ? ለምንድን ነው በምድር የምኖረው?` የእግዚአብሔር አሳብ በሕይወቴ ምንድን ነው? ይህን መልስ ማግኜት እንዳትጠፉ ይረዳችኋል። … ሌሎች በርካታ ነገሮች አሉ፤

ባንመልሳቸውም ችግር የለውም፡፡ ይህ ግን ባንመልሰው ይጎዳናል፡፡ ማንነቱን የማያውቅ ሰው በየቦታው ይቀመጣል፡፡ ማንነታችሁን ካላወቃችሁ ማንነቱን የማያውቅ ጨው ውኃ ውስጥ ገብቶ እንደሚዋኘው እና ቀልጦ እንደሚቀረው ቀልጣችሁ ትቀራላችሁ፡፡ የት መሄድ? ምን ማድረግ? እንዳለባችሁ የሚወስነው ማንነታችሁን ማወቃችሁ ነው፡፡ ማንነቴ ይህ ነው፤ የምኖረው ለዚህ ነው፤ እስካላለ ድረስ የተዝረከረከ አኗኗር ይኖረዋል፡፡``[3] ማሙሻ ፈንታ (ዶ/ር)

## ማን ነበርን?

- ሙታን _ ኤፌሶን 2፡1
- ኃጢአተኞች _ ሮሜ 5፡8
- ጠላቶች _ ሮሜ 5፡10
- ደካሞች _ ሮሜ 5፡6
- ሩቅ _ ኤፌሶን 2፡12
- እንግዶች_ ኤፌሶን 2፡12
- መጻተኞች _ ኤፌሶን 2፡19
- ያለ ክርስቶስ _ ኤፌሶን 2፡12
- ያልተገረዝን _ ኤፌሶን 2፡11
- ምሕረት ያላገኘን _ 1ኛ ጴጥሮስ 2፡10
- ጨለማ _ ኤፌሶን 5፡8
- ባሮች _ ገላትያ 4፡7

[3] ማሙሻ ፈንታ (ዶ/ር)፤ ማን ነኝ በክርስቶስ፤ ክፍል 1 ስብከት፤ AASTU-ECSF- YouTube Channel.

- በክርስቶስ ምን ሆንን?
- ሕያዋን _ ኤፌሶን 2፡4
- ጻድቃን _ 1ኛ ቆሮ 6፡11
- ከአሸናፊዎች እንበልጣለን_ ሮሜ 8፡37
- ቅርብ _ ኤፌ 2፡13
- ቤተሰብ _ ኤፌ 2፡19
- ባለአገር _ ኤፌ 2፡19
- ክርስቶስ አለን_ 1ኛ ቆሮ 8፡6
- ምሕረት አግኝተናል_ 1ኛ ጴጥ 2፡10
- ብርሃን_ ኤፌ 5፡8
- ልጆች_ ገላትያ 3፡26
- አዲስ ፍጥረት_ 2ኛ ቆሮ 5፡17

**የ_ማን_ነኝ ጥያቄ** _ የኢየሱስ (ሮሜ 1፡6 1ኛ ቆሮንቶስ 3፡23፤ 6፡19_20)

**የእርሱ ምንድን ነን?**

- አካሉ (ኤፌሶን 1፡23 1ኛ ቆሮ 6፡15፤ 12፡27)
- ባሪያዎቹ (ሮሜ 6፡19 ፊልጵ 1፡1 ቆላስ 1፡7)
- መዓዛ (2ቆሮ 2፡15)
- መልእክት (2ቆሮ 3፡3)
- ክብር (2ቆሮ 8፡23)
- ቤተመቅደስ (1ቆሮ 6፡19 የመንፈሱ)
- ቤቱ (ኤፌ 2፡22 1ጴጥ 2፡5)

- ሕንጻ (1ቆሮ 3፡9)
- እርሻ (1ቆሮ 3፡9)

``እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል የሰራቸውንና ያደረጋቸውን ታላላቅ ስራዎች የማንነት ለውጦች ለመዘርዘር እሞክራለሁ። እነርሱም፡- አዲስ ሕይወት፣ አዲስ ኅብረት፣ አዲስ ቤተሰብነት፣ አዲስ ዋስትና፣ አዲስ ርስት እና አዲስ ሥራ።``[4] ሙላቱ በላይነህ (ዶ/ር)

**ራስን በክርስቶስ መተርጎም/ማየት** _ ራስህንም ሆነ ሌሎችን በአሮጌው ታሪክ (በአዳም) መተርጎም አትችልም!

በክርስቶስ ያገኘነውን ማንነት መግለጥ ወይም በአዲሱ ማንነት መኖር ይገባል! የዚህ ጅማሬ _ ልብስ እንደሚወልቅ አሮጌውን በማውለቅ የሚከናወን ነው! (ኤፌሶን 4፡20_24 ቆላስ 3፡9_11)

በመጨረሻም **ከማንነት ተነስቶ** ፡-

_ ባሕርይን መቅረጽ (1ቆሮ 6፡19_20)

_ ምልልስን ማቅናት (ኤፌሶን 4፡1_6፡9)

_ ጠላትን መቃወም (ኤፌ 6፡10_18 እና

[4] ሙላቱ በላይነህ (ዶ/ር)፤ የወጣቱ ትውልድ ዕድሎችና ተግዳሮቶች፤ 12

_ ማገልገል (1ጴጥ 2፡10) እንደሚገባን ማስታወስ ይኖርብናል።

በርናባስ ዘመነ (B.TH, M.A)

(ታህሳስ 2016 ዓም)

**ምንጮች፡**


- ሙላቱ በላይነህ (ዶ/ር)፤ የወጣቱ ትውልድ ዕድሎችና ተግዳሮቶች፤ ሚኒሶታ፡- 2015 ዓ.ም
- ማሙሻ ፈንታ (ዶ/ር)፤ ማን ነኝ በክርስቶስ፤ ክፍል 1 ስብከት፤ AASTU-ECSF- YouTube Channel.
- ዮዲት ታሪኩ፤ ማንነት በመጽሐፍ ቅዱስ አውድ፡ በክርስቶስ ያለን ማንነት፤ የፕሮግራም ንግግር፤ Selah Ethiopia: YouTube Channel.
- Myles Munroe, Dr . 5 Questions every Human being must answer. Wordpress.com